# ፍየል ወዲህ...

## ክፍል አንድ

### በሽር አህመድ 11-26-14

ኢትዮጵያ ከደርግ ሥርዓት ተላቃ በሠላም፣ ዴሞክራሲና ልማት ጎዳና መጓዝ ከጀመረች ሃያ ሦስት ዓመታት ተቆጥረዋል። በእነዚህ ዓመታት በመላ አገሪቱ ሠላም ሰፍኗል፤ ቀጣይነት ያለው ፈጣን ልማትንም ማረጋገጥ ተችሏል። እየተመዘገበ ያለው ባለሁለት አኃዝ የኢኮኖሚ እድገት እንደሚያመላክተው በቀጣይ አሥርና አሥራ አምስት ዓመታት ውስጥ አገሪቱ ወደላቀ የእድገት ደረጃ መሸጋገሯ አይቀሬ ይሆናል።
በኢኮኖሚ የዳበረች አፍሪካዊት ኃያል አገር መሆኗ የግድ ይሆናል። ህዝቧም በአስተማማኝ መልክ ይበለጽጋል። ይህንን እውነታ ከወዲሁ የተገነዘቡ አንዳንድ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች ታዲያ የተጀመረውን ልማት ለማደናቀፍና ሠላሟን ለማደፍረስ በየጊዜው የተለያዩ ስትራቴጂዎችን እየነደፉ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ።

የስትራቴጂዎቹ መሠረት በዋናነት የአገሪቱን ልማት ማደናቀፍና ህዝቦቿን ማበጣበጥ ነው። አገሪቱን በብጥብጥና በሁከት ማስዕበል ውስጥ በማስገባት ኢትዮጵያውያንን ወደ የእርስ በርስ ግጭትና ደም መፋሰስ በማስገባት የልማት እንቅስቃሴውን ለማስተጓጎል ያለመ ነው፤ ለዚህ ማስፈፀሚያ ከሚጠቀሙባቸው ስልቶች አንዱ የኃይማኖት አክራሪነትን ማስፋፋትና በኃይማኖት ሽፋን የሽብር ተግባራትን በማቀናጀት ሰዎች በፍርሃት የእነሱን ፍላጎት ያለምንም ጥያቄ እንዲቀበሉ የማድረግ እንቅስቃሴን ነው።

የኢትዮጵያ ጠላቶች የአገሪቱን ልማት ለማደናቀፍ በሚያደርጉት ጥረት አንዱ ስልታቸው ሲከሽፍ ሌላ ስልት በመቀየር እንቅስቃሴያቸውን ይቀጥላሉ። በዚህ ምክንያት የተጠቀሙት ሌላው ስልት በአገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን በመሳሪያነት መጠቀም ነው።

በውጭ ያሉት የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሕገ መንግሥቱን በሕገ ወጥ መንገድ፣ በአመጽና በጦርነት ለመናድ አልመው እየሰሩ ያሉ ናቸው። እነዚህም በአገሪቱ ሕግ በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅትነት ለመንቀሳቀስ እውቅና ያላገኙ ግለሰቦች የተሰባሰቡባቸው ናቸው። በአገር ውስጥ ያሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በህጋዊነት የተመዘገቡና በአገሪቱ በተለያዩ ምርጫዎች የሚሳተፉ፤ የፖለቲካ አጀንዳቸውንም በነጻነት የሚያራዱ ናቸው፡፡ እነዚህ ብዙዎቹ የፖለቲካ ድርጅቶችም በሕጋዊነት ስም ሕገ ወጥ ተግባራትን የሚያከናውኑ ናቸው። ሲፈልጉ አመጽና ብጥብጥን በመፍጠር የአገሪቱን ሠላም ለማደፍረስ ይሰራሉ፤ ምርጫ በመጣ ጊዜ ደግሞ ለመመረጥ ይወዳደራሉ። ከየትኛው ወገን እንደሆኑ በግልጽ ያልለየላቸው ግን ሁለቱን ተግባራት በግላጭ የሚፈጽሙ ናቸው።

በውጭ አገራት እየኖሩ አገር ውስጥ ብጥብና ሁከት እንዲፈጠር የሚያደርጉ ቡድኖች አገር ውስጥ በሕጋዊነት ስም ከሚንቀሳቀሱት ጋር ለጥፋትና ለሽብር ተልዕኳቸው ግንባር ፈጥረው የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታም ይስተዋላል። የኢትዮጵያን ልማት የማይፈልጉ ወገኖች ከእነዚህ የፖለቲካ ድርጅት ነን ባዮች ጋር በመቆራኘት በገንዘብ፣ በሥልጠናና በሌሎች አስፈላጊ ነገሮች ድጋፍ በማድረግ ፓርቲዎቹ የአገራቸውን ልማት ለማደናቀፍና የህዝባቸውን ድህነት ለማባባስ እንዲነሱና መሰናክል እንዲሆኑ የማድረግ አቅጣጫን ይከተላሉ - የኢትዮጵያ ጠላቶች።

እነዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች በዓለም አቀፍ አሸባሪዎችና እነሱን ከሚደግፉ መንግሥታት በሚያገኙት ገንዘብ የአገሪቱን ሠላም ለማደፍረስ ሲንቀሳቀሱ ይስተዋላሉ። በአገራቸውና በህዝባቸው ላይ ክህደትንና ጥፋትን ሲፈጽሙም ይታያሉ። ፖለቲካንና ኃይማኖትን በማደበላለቅ የፖለቲካ አጀንዳን በኃይማኖት ሽፋን እውን ለማድረግ በአንዱ ካልተሳካ ሌላውን በመጠቀም በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። በአገራችን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየሰፋ የመጣው የኃይማኖት አክራሪነትም ከዚሁ ፍላጎት የመነጨ ነው። በተለያዩ አካባቢዎች በተለያዩ የእምነት ተቋማት በመደበቅና በአማኞች መካከል  አማኝ መስሎ ሰርጎ በመግባት ቀላል የማይባል የጥፋት ድርጊቶችን ሲያከናውኑ ቆይተዋል። በዋናነት ከሚሰሩበት ዘዴ

አንዱ ከሁሉም በፊት በአገሪቱ ብጥብጥና ደም መፋሰስን መፍጠርና ሠላምን ማደፍረስ ነው።
ሠላምን በማደፍረስና ሁከትን በመፍጠር በግርግር ያሰቡትን የፖለቲካ አጀንዳ ማሳካት ያስችላል ብለው ያምናሉ። በዚህ መልክ ካደረጓቸው እንቅስቃሴዎች አንዱ በተለያዩ ኃይማኖት አማኞች መካከል ግጭትን መፍጠር ነው። በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ያዋጣል ብለው የጀመሩትም በክርስትናና በእስልምና ኃይማኖት አማኞች  መካከል መቃቃርንና ብጥብጥን  መፍጠር ነበር። ይህንን ለማሳካት ከፊል አባሎቻቸው የእስልምና እምነት አለባበስን ለብሰው የክርስትና እምነት ተከታዮች ኃይማኖታዊ ተልዕኮ ለማድረስ በሚሰበሰቡበት ወቅት  በቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ እየገቡ የእስልምና ኃይማኖት ተልዕኮ አፈጻፀም ድምፀትንና ፀሎትን በማሰማት ብጥብጥ እንዲፈጠር የማድረግ አቅጣጫ  ነበር የተከተሉት።

ሌሎች አባሎቻቸው ደግሞ በተመሳሳይ መልኩ የክርስትና ኃይማኖት አልባሳትን እየለበሱ ህዝበ ሙስሊሙ በሚሰባሰብባቸው መስጊዶች በመገኘት አስፈላጊ ያልሆኑ ጩኸቶችን በማሳማት በህዝበ ሙስሊሙና በህዝበ ክርስቲያኑ መቋጫ የሌለው ግጭትን ለመፍጠር ያልተቆጠበ ጥረት አድርገዋል። የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሽብርተኞች ይህንን ስትራቴጂ ሲነድፉ አንድም ህዝቡ ለኃይማኖቱ ቀናኢ በመሆኑ በኃይማኖት ስም ከተንቀሳቀስን ሊበርድ ወደማይችል ግጭትና ደም መፋሰስ እናስገባዋለን በሚል ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት በኃይማኖቶች መካከል የሚፈጠረውን ግጭት ለማርገብ፣ ሥርዓት ለማስያዝ፣ ለማረጋጋትና ሠላምን ለመፍጠር ሲል ሊወስድ የሚችለውን ሕጋዊ እርምጃ በማጋነንና በኃይማኖት ጣልቃ የገባ በማስመሰል መንግሥትንና አማኞችን የማለያየት እድል ይፈጥርልናል በሚል እምነት ነው። ይህንን ዓላማ አንግበው በቤተክርስቲያን ኃይማኖታዊ ተልዕኳቸውን ለመወጣት በተሰበሰቡ ምዕመናን ፊት በመሄድ የእስልምና ኃይማኖት ፀሎት በማድረግ ህዝቡ እንዲቆጣና አምርሮ በሌላ ኃይማኖት ተከታዮች ላይ እንዲነሳሳ ለማድረግ ያልበጠሱት ቅጠል ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም።

በዚህች አገር ኃይማኖታዊ ጦርነት እንዲቀሰቀስ ያልተቆጠበ ጥረትና እንቅስቃሴ አድርገዋል፤ ረጅም ርቀትም ተጉዘዋል። በዚህ መልክ ባደረጉት ሰፊ እንቅስቃሴ ቀላል የማይባል ጉዳት አድርሰዋል። በኃይማኖት ሽፋንም በርካታ ለኃይማኖታቸው ቀናኢ የሆኑ ንጹኃን አማኞችን አሳስተዋል። በአገር ውስጥ ያሉ አንዳንድ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ለችግሩ መባባስ ቀላል የማይባል ድርሻ እንደነበራቸውም ይታወቃል። መቀመጫቸውን በውጭ አገራት ያደረጉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ነን ባይ አሸባሪዎችን እነሱ በሞቀ ቤት ተቀምጠው ጨቅላ ወጣቶችን በገንዘብ እየደለሉ አገር ውስጥ በሕገ ወጥ ተግባር እንዲሰማሩ ያደረገ አቅጣጫን ይከተላሉ። በዚህ መልክ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ አመራር ነይ ባዮችን አስመልክተው ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ ያሉት ነገር ነበር።

“አንድ ሕዝብን አስተዳድራለሁ፤ ለህዝብ ቆሜያለሁ የሚል ፖለቲከኛ ወይም የፖለቲካ አመራር ራሱ ሊገባበት የማይፈልገውንና በራሱ እንዲደርስ የማይሻውን ምንም የማያውቁ ለጋ ወጣቶችን በገንዘብ እያታለለ መማገድ ከተጠያቂነት አያድንም፤ ሞራላዊም ሕልናዊም አይደለም።” ነበር ያሉት። እርግጥ ነው ራሳቸውን ከችግር አርቀው በአገሪቱ የሚገኙ ወጣቶችን በሕገ ወጥ መንገድ እንዲንቀሳቀሱ እያደረጉ ያሉ ወገኖች በሌሎች ደም መጫወት እንደሆነ እሙን ነው።

አገር ውስጥ ሆነው እነሱም እየተሳተፉበት መንቀሳቀስና ለሚነሳ ተጠያቂነትም ሆነ ችግር በእምነት መጋፈጥ ሲገባቸው በውጭ አገራት ሆነው ገንዘብ በመላክና ወጣቱን በማታለል ቁጥራቸው ቀላል ያልሆነ ወጣቶች፣ ሴቶችና አባቶች በማያውቁት ነገር ገብተው ለወንጀልና ለጥፋት እንዲዳረጉ ማድረግ አንድ ሕሊና ካለው ወይም አገርን እመራለሁ ከሚል ዜጋ የሚጠበቅ ነገር አይደለም።

አንዳንዶቹም ለኃይማኖታቸው ካላቸው ቀናኢነት አንጻር እየተታለሉ ከኃይማኖት ጋር ተቀላቅሎ የተነሳው ነገር ኃይማኖታዊ ጥያቄና ተልዕኮ ያዘለ መስሏቸው ባላወቁት ጉዳይ ለፖለቲከኞች ህቡዕ አጀንዳ መፈፀሚያ መሣሪያ ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው።

ቤተክርስቲያኖችንና መስጊዶችን በማቃጠል፣ የኃይማኖት መምህራንና አባቶችን በመግደልና ሌሎች  ወንጀሎችን በተለያዩ የእምነት ተከታዮች ላይ በመፈፀም ድርጊቶቹን አንድም መንግሥት የፈፀማቸው አድርገው በተለያዩ ፍትሃዊነት የጎደላቸውና በእነሱ የሚመሩ ሚዲያዎች በማስተጋባት መንግሥትን ከእምነት ተከታዮች ጋር የማቆራቆስ ስልትን በመከተል ሠላምን ለማደፍረስ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ። የተለያዩ እምነት ተከታዮችን ከመንግሥት ጋር ለማጣላት የሚደረገው ጥረት ቀጥሎ በተለይ ደግሞ በእስልምና ኃይማኖት ጫፍ የወጣበት ሁኔታ ላይ ይገኛል።  በኃይማኖታዊ መቻቻል ለዓለም ተምሣሌት የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ በኃይማኖት መካከል መቃቃርን ለመፍጠር የተደረገውን ጥረት አክሽፎታል። በአገሪቱ ለዘመናት የዘለቀው መቻቻል በቀላሉ በጥቂት ጽንፈኞች ፍላጎት ሊበጠስ አልቻለም። የኃይማኖት እኩልነት በተረጋገጠባት አገር ኃይማኖታዊ ጦርነትን ለማቀጣጠል የሚያመች መሠረት የለም።

ከዚህ የተነሳ በተለያዩ ኃይማኖት አማኞች መካከል መቋጫ የለሽ ግጭት ለመፍጠር የተደረገው እንቅስቃሴ ውኃ ባለመቋጠሩ ሽብርተኞቹ ሌላ መላ መፈየድ የግድ ሆነባቸው። እናም ፊታቸውን ወደ እስልምና ኃይማኖት በማዞር በህዝበ ሙስሊሙ መካከል የእርስ በርስ ግጭት ለመፍጠር አቅደው መንቀሳቀስ ጀመሩ። የእስልምና ኃይማኖት አማኞች እርስ በርሳቸው ተጋግዘው የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው። በመካከላቸው ያለው የአብሮነት ገመድም ጠንካራ በመሆኑ በቀላሉ የሚበጠስ አይደለም። ከሌላ እምነት ተከታዮች ጋር እንዳለው ቁርኝት ሁሉ የእርስ በርሱ ትስስርም ጠንካራ በመሆኑ የተፈለገውን አፍራሽ ውጤት ማግኘት አልተቻለም።

ከዚህ የተነሳም የቀቢፀ ተስፋ እርምጃዎችን የመውሰድና ሰዎችን በፍርሃት የተባለው ሁሉ ይቀበላሉ የሚል እምነት ይዞ መኳዝን ነበር ሽብርተኞቹና ጽንፈኞቹ የመረጡት። የተለያየ እምነት ያላቸው ኢትዮጵያዊያንንም ሆነ በተመሳሳይ እምነት የሚኖሩ ዜጎችን ማነጣጠል በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የማይታሰብ ጉዳይ ነው። በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል የማይፈለቀቅ ቁርኝትና የማይፈርስ አንድነት በመኖሩ የተነሳ ከኃይማኖት ልዩነት ጋር ተያይዞ የተፈጠረ ወይም ሊፈጠር የሚችል ክፍተት ባለመኖሩ ምክንያትና በአገሪቱ የኃይማኖት እኩልነት በመረጋገጡ የተነሳ

የኃይማኖት ጦርነት ማስነሳትም ሆነ የአረብ አገራቱ ዓይነት አመጽ ማነሳሳት የማይቻል ሆኖ አገኙት።

ከዚህ የተነሳ የሽብር ቡድኖቹ ተስፋ ቆረጡ። የኃይማኖት አባቶችን መግደልና ትላልቅ የአገሪቱ የልማት ተቋማት ላይ አነጣጥሮ መስራትን  እንደ አንድ ሌላ አማራጭ አድርገው በመውሰድ እንቅስቃሲያቸውን ቀጠሉ።  በዚህ የቀቢፀ ተስፋ የተጎዱ ንጹኃን ዜጎች በርካታ ቢሆኑም ከመጀመሪያው አቅደው ይዘውት የተነሱትን አገሪቱን መቋጫ ወደሌለው ብጥብጥና ደም መፋሰስ ለማስገባት ግን አልቻሉም።

መንግሥት ከሚያደርገው የተጠና እንቅስቃሴ ባሻገር ኅብረተሰቡ ለዚህ ሁኔታ አመቺነት አልነበረውም። የተፈጠረው የኃይማኖት እኩልነትና ነጻነትም ለእንደዚህ ዓይነት መሠረት የለሽ ብጥብጥ አጋዥ አልሆነም። ሁኔታው ተስፋ ስላስቆረጣቸው የሽብር ተግባራትን በማስፋፋት በርካቶችን ለህልፈተ ህይወት ዳረጉ። ቀላል የማይባሉ መስጊዶችና የእምነት ቦታዎች አቃጠሉ። በኃይማኖት አባቶች ላይ ቁጥር ስፍር የሌለው ዛቻ፣ ድብደባና ግድያ አደረሱ። እነዚህ አሸባሪ ቡድኖች ራሳቸውን በፖለቲካ ስም አደራጅተው መንቀሳቀስን ያቀዱት ይህንን ያህል ጥረት አድርገው የአገሪቱን ሠላም ማደፍረስም ሆነ  አንድነቷን ማፈራረስ ባለመቻላቸው ነበር።

በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ስም በመደራጀት ቀደም ሲል የተገለፀው የአገሪቱን ሠላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ የማደናቀፍና ተግባራቸውን ለማሳካት ቆርጠው ተነሱ። በፖለቲካ ድርጅት ስም መንቀሳቀስ የጀመሩት ሽብርተኞች በዚህ ስልታቸው አባላትን በሰፊው መመልመል ችለዋል። የመለመሏቸውን አባላት በአገር ውስጥና በተለያዩ የውጭ አገራት በመውሰድ የሽብር ተግባር አፈጻፀም ሥልጠናዎች እንዲያገኙ አድርገዋል። በዚህ መልክ አባሎቻቸውን ካስታጠቁ በኋላ ነው በተለያዩ ቦታዎች የተቀናጀ የሽብር ተግባራትን ለመፈፀም መንቀሳቀስ የጀመሩት።

በዚህ መልክ ከአገር ውስጥና ከውጭ አገራት የአገራችን ጠላቶች ጋር ጥብቅ ቁርኝት በመፍጠር ለእኩይ ምግባራቸው የሚውል ማንኛውንም ድጋፍ በማግኘት መንቀሳቀስን የመረጡት ሽብርተኞች አሁንም ይህንን ተግባራቸውን ለመፈፀም

በተለያየ   መልክ እየተንቀሳቀሱ ይገኛል። እነዚህ በፖለቲክ ፓርቲ ስም እየተንቀሳቀሱ ያሉ ሽብርተኞች ኦነግ፣ አብነግና ግንቦት ሰባት የሚባሉት በውጭ አገራት ሆነው የሚንቀሳቀሱና የኢትዮጵያ መንግሥትም በሽብርተኝነት የለያቸው ቡድኖች ናቸው።

እነዘህ ቡድኖች በተለያየ ጊዜ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በሚኖሩ ንጹኃን ዜጎች ላይ ጉዳትን ለማድረስ ተንቀሳቅሰዋል። ቀላል የማይባል ጉዳትም አድርሰዋል። በአገራችን የተለያዩ አካባቢዎች እየተዘዋወሩ አንዱን ብሔር በሌላው ለማነሳሳት ያልተቆጠበ ጥረትን አድርገዋል። ለአብነት ያህል በኦሮሚያ፣ በሶማሌና በጋምቤላ ክልሎች ከሌላ ክልል ሄደው በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና በክልሉ ተወላጆች መካከል ግጭትን ለመፍጠር ተንቀሳቅሰዋል። የንጹኃን ዜጎች ደምም ያለአግባብ ፈሷል። በፈፀሟቸው የሽብር ተግባራት ተጎጂ የሆኑ ዜጎች በመንግሥት እንዲያማርሩ ለማድረግ ጥረዋል።

ለሰዎች ህይወት የማይሳሱት የሽብር ቡድኖች በአንዳንድ አካባቢዎች ጅምላ ጭፍጨፋ አካሂደዋል። በህዝብ መጓጓዣዎች ላይ ጥቃትን ፈጽመዋል። ከዚህም አልፈው በገበያ ቦታዎችና በህዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች ላይ  ተደጋጋሚ ጥቃቶችን አቀነባብረዋል። ቤተክርስቲያኖችን፣ መስጊዶችንና ትምህርት ቤቶችን ሳይቀር አቃጥለዋል። ከዚህም አልፈው በመንግሥት ትላልቅ ፕሮጀክቶች የተነጣጠሩ የሽብር ተግባራትን ለመፈፀም ያልተቆጠበ ጥረት ያደረጉ ቢሆንም በፀጥታ ኃይሎችና በኅብረተሰቡ ትብብር ያሰቡትን ማሳካት  አልቻሉም።

በተለያየ ጊዜ ለመፈፀም ያቀዷቸው የተለያዩ የሽብር እቅዶች በኅብረተሰቡ ጥረት ከሽፋዋል። የዚህ እንቅስቃሴ መክሸፍን በተገነዘቡ ወቅትም ተስፋ ቆርጠው አርፈው አልተቀመጡም። ሌላ ስልት መቀየስን መረጡ እንጂ። ቡድኖቹ ሌላ የተጠና የሽብር ተግባር መፈፀሚያ መሣሪያ ይሆናል ያሉትን ይዘው በሌላ መልክ ብቅ ማለትን ነበር የመረጡት። በዋናነት አገር ውስጥ እየተንቀሳቀሱ የሚገኙ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን ሙሉ በሙሉ የሽብር ፈጻሚ አካላት ማድረግን ማዕከል

ያደረገ እንቅስቃሴ ፈፀሙ። ይህ እንቅስቃሴያቸው በተወሰነ ደረጃ ውጤት ያስገኘላቸው ተግባር ነበር።

በአገሪቱ ያለውን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በማጣጣልና ጥላሸት በመቀባት የጀመረው የእነዚህ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ውሎ እያደረ ሲመጣ ደግሞ በቀጥታ በሽብር ተግባራት የሚሳተፉበት ሁኔታ በማመቻቸት ቀጥተኛ የሆነ የሽብር ተግባርን መፈፀሙን ተያይዘውታል።

መንግሥት በአገሪቱ ሊደርሱ ከሚችሉ የሽብር ተግባራት ለመከለከልና በደረሱበት ወቅትም በሕግ ለማስተናገድ ባለው ቁርጠኝነት መሠረት በሕግ አውጪው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፀረ ሽብር ሕግ ወጥቶ እንዲፀድቅ አድርጓል። በኢትዮጵያ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ከተዘረጋ ሁለት አሥርት ዓመታት አልፈዋል።

በአገሪቱ የተፈጠረው ምቹና ሰፊ የፖለቲካ ምህዳር በመጠቀምም ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ተመሥርተው የፖለቲካ አጀንዳቸውን ለማሳካት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። ባለፉት ሃያ ሦስት ዓመታት በየአምስት ዓመቱ በተካሄዱ አራት ምርጫዎች ላይ እነዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች የነበራቸው ተሳትፎ የጎላ እንደነበር እሙን ነው።

ይሁንና አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች የአገሪቱ ሕገ መንግሥት በሚፈቅደው መሠረት የህዝቡን ይሁንታና ድጋፍ ለማግኘት ጥረት እያደረጉ እንዳሉ ቢታወቅም በተቃራኒው አንዳንድ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ደግሞ በሕጋዊ የፖለቲካ ድርጅት ስም ሕገ መንግሥቱን ሲተላለፉ ይታያሉ።

የዜጎችን መብትና እኩልነት ያረጋገጠውና ዜጎች በፈለጉት የፖለቲካ ድርጅት ያለምንም ተጽእዕኖ ተደራጅተው እንዲሳተፉ ሙሉ ነጻነታቸውን ያጎናፀፈን የአገሪቱ የበላይ ሕግ የሆነው ሕገ መንግሥት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ለመናድ ያለመ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ይስተዋላሉ። ህልውናው የፈጠረላቸውንና በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ ያስቻላቸውን የአገሪቱን ሕገ መንግሥት አክብረው መንቀሳቀስና

የፖለቲካ አጀንዳቸውን በሕዝብ በማስረፅ በምርጫ አሸንፈው ወደ ኃላፊነት መምጣት የሚያስችላቸውን ቀና መንገድ ከመከተል ይልቅ ይህ ነው የሚባል አጀንዳ ሳይዙና በሕዝቡ መካከል ሁከትና ትርምስን በመፍጠር በግርግር ለመጠቀም አልመው በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሕገ መንግሥቱን ሲተላለፉ ይስተዋላሉ ።

በቀደሙት ዓመታት በአገራችን የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የሚያራምዷቸው ሕጋዊነት የጎደላቸው ተግባራት በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ጥያቄ ያስነሱ እንደነበሩ ይታወቃል። በተለይም አገራችን የሚታካሂዳቸውን ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶችን በማጣጣልና ተገቢ ያልሆነና የተዛቡ አስተያየቶችን በመስጠት የአገሪቱን ብሄራዊ ድህነንት ሊፈታተኑ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ውሣኔዎችን በመቃወምና ከአገሪቱ የውጭ ጠላቶች ጋር በማበርና በመተጋገዝ የተሳሳተ መንገድ ሲሄዱ መስተዋላቸው ይታወቃል።

በዚህ ጽሁፍ ልዩ ትኩረት ሰጥተን የምናየው በቀደሙት ዓመታት የተከናወኑ ድርጊቶችን ሳይሆን ከተቋቋመ ገና ሁለት ዓመት ያልሞላው ሰማያዊ ፓርቲ በመባል የሚታወቀው ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት እያደረገ ያለውን አፍራሽ እንቅስቃሴን ነው። የቀደሙት ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን ትተን ከሁለት ዓመት ያነሰ ዕድሜ ባለው በ"ሰማያዊ ፓርቲ" ላይ ማነጣጠራችን ይህ ፓርቲ ከተቋቋመበት እለት አንስቶ እስካሁን ድረስ በተለያየ ጊዜ በአገራችን የሚነሱ ወቅታዊ ሁነቶችን መሠረት እያደረገ ሕቡዕ አጀንዳውን ለማሳካት ያልተቆጠበ ጥረት እያደረገ በመሆኑ ነው።

ይህ ፓርቲው የተቃውሞ እንቅስቃሴውን የጀመረው የፖለቲካ አጀንዳውን ነድፎ ለሕዝብ በማስተዋወቅና ሌሎች ፓርቲዎች ጋር ያለውን ልዩነትና አምስሎ ለሕዝብ በማስረፅ አልነበረም። ቀድሞውንም የተነደፈ የፖለቲካ አጀንዳ የለውም።

ሰማያዊ ፓርቲ በሕዝብ ዘንድ የፖለቲካ ተቀባይነትን ለማግኘት በአገሪቱ ሕገ መንግሥት መሠረት መንቀሳቀሱን ወደጎን በመተው ርካሽ ተወዳጅነትንና

በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ወቅታዊ አጀንዳ እያንጠለጠለ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ፓርቲ  መሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም። ገና ፈቃዱን አግኝቶ በአገሪቱ መንቀሳቀስ ከመጀመሩ ማግሥት ተቃውሞውን የጀመረው  የአገሪቱን የህዳሴ  ጉዞ ለማፋጠን ወሣኝ ሚና ባላቸው ትላልቅ የአገሪቱ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ ነበር።